# በአማራ ክልል ከ700 በላይ የህብረት ስራ ማህበራት ተቋቋሙ

በአማራ ክልል በተጠናቀቀው የበጀት አመት ከ700 በላይ ማህበራት መቋቋማቸውን የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ሃላፊ አቶ አየነው አሰፋ ለጋዜጣው ሪፖርተር እንደገለፁት ባለፈው የበጀት አመት 332 ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራትና 268 ከሁለገብ ውጭ ያሉ የገንዘብ ቁጠባ፣ የመስኖ፣ የብድር፣ የዕጣንና ሙጫ፣ የመኖሪያ ቤትና የዕደ ጥበብ ማህበራት ተቋቁመዋል።

በአመቱ 14 ዩኒየኖች የተመሰረቱ ሲሆን ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃር በ12 ብልጫ እንዳላቸውም አቶ አየነው ተናግረዋል።

በክልሉ በአሁኑ ወቅት 208 ሺህ 930 ነባር እና 7 ሺህ 256 አዲስ የቤተሰብ ሃላፊዎች በህብረት ስራ ማህበራት መታቀፋቸውን የገለፁት ሃላፊው ይህም በክልሉ ይኖራሉ ተብለው ከሚገመቱት የቤተሰብ ሃላፊዎች ውስጥ 44 በመቶ እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸውን ለማሳደግ ከ1 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ማህበራት የተለያዩ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን ሃላፊው ጠቁመዋል።

ነባሮቹና አዲሶቹ ዩኒየኖች ከ23 ሚሊዮን ብር በላይ፣ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ደግሞ ከ74 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ይዘው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል። በበጀት አመቱ 10 ነባር ዩኒየኖች 5 ሚሊዮን ብር አትርፈው በራሳቸው ውሳኔ ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ ለአባላት ማከፋፈላቸውንም አቶ አየነው ገልፀዋል።

በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል 1 ሺህ 800 የህብረት ስራ ማህበራትና 24 ዩኒየኖች ከ98 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ካፒታል እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ከአቶ አየነው ገለፃ ለመረዳት ተችሏል። ጰ